**የንግድ ምክር ቤቶች የሺሚነት ሥልጣን ሚና።**
**(በዮሐንስ ወልደገብርኤል)**

በመላው ዓለም የሚገኙ አብዛኞቹ የንግድ እና ኢንዱስትሩ ምክር ቤቶች አብይ ኃላፊነቶች ውስጥ የግልግል ዳኛ ሺሚ አካል ሆነው ማገልገል በስፋት የተለመደው ተግባራቸው ነው። ብዙውን ጊዜ በተዋዋይ ነጋዴ ወገኖች እና/ወይም ደንበኞቻችው ውሎች የሚመነጩ አለመግባባቶች የሚፈቱት በግልግል ወይም በአማራጭ የውዝግብ መፍቻ ስልቶች መሆኑ ይታወቃል። በተለያዩ ተጨባጭ እና ተግባራዊ ምክኒያቶች ነጋዴዎች ሰላማዊ እና ሙግት የማይበዛበት የውዝግብ አፈታት ስልቶችን ከመምረጥ ባሻገር በተቻላቸው መጠን ጉዳዮች ወደፍርድ ቤት ላለመምራት ራሳቸውን ያቅባሉ።

እንደ ህጋዊ ዘላቂነት እና ተቀባይነት ያለው፣ አስተማማኝ እና እምነት የሚጣልበት የንግዱ ማህበረሰብ ማህበር በአብዛኛው ሰላማዊ የውዝግቦች መፍቻ መድረኮችን የማመቻቸት እና በግልግል፣በማግባባት፣ በማስማማት እና በአድጁዲኬሽን አለመግባባቶችን ለመፍታት የሚሾሙ አግባብነት ያላቸውን ሙያተኞች የመሾም ኃላፊነት የሚሰጠው በአብዛኛው ለንግድ ምክር ቤቶች ነው። በዚህም መሰረት ተከራካሪ ወገኖች የግልግል ዳኛ እንዲሾምላቸው ብዙውን ጊዜ ጥያቂያቸውን የሚያቀርቡት ወይም ድጋፍ የሚጠይቁት የንግድ ምክር ቤቶችን ነው።

ይሁን እንጂ ሁሉም የንግድ ምክር ቤቶች ኃላፊነታቸውን ለመወጣት አንድ ዓይነት ደንቦች፣ልምዶች እና ስርዓቶች ላይኖሯቸው ይችላል።በኢትዮጵያ ተቋቁመው እያሰሩ ከሚገኙ የንግድ ምክር ቤቶች ቀደምት እና አንጋፋ የሆነው የአዲስ አበባ ንግድ እና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በውዝግቦች ላይ መፍትሔ ለመስጠት የሚሰማሩ የግልግል ዳኞች፣አግባቢዎች፣አስማሚዎች እና አድጁዲኬተሮች አሿሿም ላይ በጣም የተብራሩ ደንቦች፣ስርዓቶች እና ልምዶች አሉት። በአሁኑ ወቅት የአዲስ አበባ ንግድ እና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ለውዝግቦች ሰላማዊ መፍትሄ የሚሰጡ ሙያተኞች ሿሚ አካል ተደርጎ በውሎች ወይም በህግ የተሰጠውን ኃላፊነት የሚያስፈፅመው የተሟላ አሰራር ነፃነት ያለው ሆኖም የምክር ቤቱ አካል በሆነው የግልግል ተቋሙ ነው። ይህ ፁሁፍ በውዝግብ አፈታት ላይ የሚሰማሩ ሙያተኞች አሰያየም እና አሿሿም ኃላፊነቱን የአዲስ አበባ ንግድ እና የዘርፍ ማህበራት የግልግል ተቋም እንዴት እንደሚያስፈፅመው ዳሰሳ ያደርጋል።

የአዲስ አበባ ንግድ እና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የግልግል ተቋም ከሚሰጣቸው አገልግሎቶቹ ውስጥ የግልግል ዳኞች፣ አግባቢዎችን፣ አስማሚዎችን እና አድጁዲኬተሮችን መሾም በተደጋጋሚ ከሚያከናውናቸው አገልግሎቶች ውስጥ ይጠቀሳሉ። በርካታ የንግድ ውሎች በግለሰቦች፣ በግል ድርጅቶች እና በመንግስት ተቋማት ሲዘጋጁም ሆነ ሲፈረሙ የንግድ ምክር ቤቶች በአጠቃላይ የአዲስ አበባ ንግድ እና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት በተለይ የግልግል ዳኞችን፣ አግባቢዎችን፣ አስማሚዎችን እና አድጁዲኬተሮችን ሿሚ አካል የሚያደርግ ድንጋጌዎችን ያካትታሉ። ይህ አይነቱ አቀራረፅ በተለይም ውዝግቦችን በግልግል እና በአድጁዲኬሽን የመፍታት ልምዶች በስፋት በሚታይባቸው በግንባታ ውሎች ላይ የተለመደ ነው። ቀድሞ የመንግስት የግዢ ኤጀንሲ ሲባል የነበረው እና አሁን የመንግስት የግዢ እና የንብረት አሰተዳደር ኤጀንሲ ተብሎ የተሰየመው ተቋም በሚያዘጋጃቸው አብዛኛው የግንባታ ውሎች ጠቅላላ እና ልዩ የውል ሁኔታዎችን የሚጠቀሙ የአዲስ አበባ ንግድ እና የዘርፍ

ማህበራት ምክር ቤት የግልግል ተቋምን የግልግል ዳኛ ወይም አድጁዲኬተር ሿሚ ባለስልጣን በማድረግ ይሰይማሉ፡፡

የአዲስ አበባ ንግድ እና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የግልግል ተቋምም በዚህ ረገድ ለደንበኞቹ የሚሰጠው አገልግሎት ግልፅ ተደራጀ እና ተጠያቂነት ከሰፈነባቸው አገልግሎቶቹ አንዱ የግልግል ዳኞችን፣ አድጁዲኬተሮችን፣ አግባቢዎችን እና አስማሚዎችን የመሾም አገልግሎቱ ነው፡፡ የግልግል ተቋሙ በግልግል ዳኝነት እና በሌሎች አማራጭ የውዝግብ አፈታት ላይ የሚያገለግሉ የተለያዩ ሙያተኞችን ስም ዝርዝር እና መረጃዎችን የያዘ የባህር መዝገብ አደራጅቷል፡፡ ይህ የባህር መዝገብ እና የሙያተኞች ዝርዝር ምክር ቤቱ እና ተቋሙ አገልግሎቱን መስጠት ከጀመረበት ጊዜያት አንስቶ ለዓመታት ሲያደራጁት የቆየ ነው፡፡ አብዛኞቹ ሙያተኞች ተገልጋዮች አገልግሎታቸውን ሲጠይቁ የሚሾሙ እና ተቋሙ በሚያከናውናቸው ተቋማዊም ሆኑ ጊዚያዊ የግልግል እና አማራጭ የውዝግብ አፈታት አገልግሎቶች ላይ እየተሰየሙ አገልግሎት ሲሰጡ የነበሩ ናቸው፡፡ እነኚህ ሙያተኞች የአዲስ አበባ ንግድ እና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የግልግል ተቋም በሚያዘጋጃቸው በርካታ ስልጠናዎች እና አውደጥናቶች ላይም የተሳተፉ ናቸው፡፡

የተቋሙ የባህር መዝገብ በየጊዜው ወቅታዊነቱን እንዲጠብቅ የሚደረግ እና በተቋሙ ከፍተኛ አካል በሆነው የግልግል ተቋሙ ካውንስልም የጸደቀ ነው፡፡ የባህር መዝገቡ የግልግል ተቋሙ ለሚያደርገው የግልግል ዳኞች እና የሌሎች የውዝግብ አፈታት ስልቶች ሙያተኞች ማለትም የአግባቢዎች፣የአስማሚዎች እና የአድጁዲኬተሮች አሿሿም ይፋዊ መሰረት ነው፡፡ ይሁን እንጂ አልፎ አልፎ ተቋሙ በባህር መዝገቡ ላይ ከተዘረዘሩት ሙያተኞች ውጪ ሊሾም ይችላል፡፡ በጊዚያውም ሆነ በተቋማዊ የግልግል እና የሌሎች አማራጭ የውዝግብ አፈታት ስልቶች የሚሾሙ የግልግል ዳኞች እና ሌሎች ሙያተኞች አሿሿም ሥነ ስርዓት ሁሉም አንድ ዓይነት ነው፡፡ እያንዳንዱ ተሿሚ የግልግል ዳኝነትን ስለመቀበሉ እና ከማንኛውም ተከራካሪ ወገን፣ከጠበቆቻቸው እና ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ አስቀድሞ ምንም ዓይነት ዝምድና፣ግንኙነት እና ጥቅም ነፃ መሆኑን ከንግድ ምክር ቤቱ የግልግል ደንብ ጋር የተያያዘውን ቅፅ በመሙላት መግለጫ እና ማረጋገጫ መስጠት ይጠበቅበታል፡፡

ይህ ቅፅ ተሰያሚው ወይም ተሿሚው የአዲስ አበባ ንግድ እና የዘርፍ ማህበራት አግባብነት ያላቸውን ደንቦች እና የስነ ምግባር ህግጋትን እንዲያከበር፣ከማንኛውም ተከራካሪ ወገን ገንዘብ ላለመቀበል እና ከየትኛውም ወገን እና ከጉዳዩ ጋር ነፃ መሆኑን የሚያረጋግጥ የተሟላ እና ትክክለኛ መግለጫን እንዲሰጥም ያስገድደዋል፡፡

የተሿሚው የግልግል ዳኝነትን ስለመቀበሉ እና ነፃ መሆኑን ፈርሞ የሚያረጋግጥበት ቅፅ ከተሞላ በኃላ ለሁሉም ተከራካሪ ወገኖች ተልኮ እንዲመረመር እና አስተያየታቸውንም እንዲሰጡበት ይደረጋል፡፡ ተከራካሪ ወገኖች ምንግዜም የበኩላቸውን አስተያየታቸውን በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ በፁሁፍ እንዲሰጡ ይበረታታሉ፡፡ በተጨማሪም ተከራካሪ ወገኖች አግባብነት ያለውን ህግ ተከትለው በተሿሚው መግለጫ እና በማረጋገጫ ላይ እና ተሿሚው የተሰየመበትን ጉዳይ እንዳያከናውን የሚያግደው ሁኔታ ካለ ተቃውሟቸውን እንዲያቀርቡም ይመከራሉ፡፡

ተከራካሪ ወገኖች የፁሁፍ አስተያየታቸውን ወይም መቃወሚያቸውን በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ የማያቀርቡ ከሆነ ግን አስተያየት ወይም ተቃውሞ እንደሌላቸው ተቆጥሮ ተቋሙ ሹመቱ

ተቀባይነት ያገኘ መሆኑን የሚገልፅ ደብዳቤ ይሰጣል፡፡ይሁን እንጂ ተቋሙ ፍትህን ሊያዛቡ የሚችሉ ከተሿሚው ጋር የተያያዙ መልካም ያልሆኑና ያልተገቡ ባህሪያት ጋር ማናቸውንም የሚቀርቡ መረጃዎችን፣ቅሬታዎችን ምንግዜም የሚቀበል ሲሆን አስፈላጊ ሲሆን አግባብነት ያላቸው ህጎች ሊጣሱ ይችላሉ ብሎ ሲያምን ተገቢው እርምጃ እንዲወስድ ያደርጋል፡፡ ለምሳሌ ለተቋሙ በቀረበ በአንድ የግልግል ጉዳይ ላይ በአንድ ተከራካሪ ወገን ተሰይሞ የተሾመ የግልግል ዳኛ በግልግል ዳኛነቱ በመስራቱ አገኛለሁ ብሎ ያሰበው ከፍተኛ የአበል መጠን እና በምክር ቤቱ ህግ መሰረት የሚከፈለውን በተጨባጭ ከተረዳ በኃላ በተሰማው ቅሬታ ምክኒያት በተደጋጋሚ ከግልግል ጉባኤው መቅረቱ በመረጋገጡ ምክኒያት ለተቋሙ በቀረበው መረጃ መሰረት ቅሬታ ባደረበት የግልግል ዳኛ ላይ ወዲያውኑ እርምጃ እንዲወሰድ ተደርጓል፡፡

በአሰያየም እና በመቀጠልም በአሿሿም ሂደት ተቋሙ በተቻለ መጠን ፍትሐዊነት ለማረጋገጥ የሚሞክር ሲሆን በተለይም ማህበራዊ እና ሙያዊ የስነ ምግባር ግዴታቸው አድርገው በመውሰድ ነፃ አገልግሎቶችን ለሚሰጡ ሙያተኞች ድካማቸውን ለማካካስ ቅድሚያ ይሰጣል፡፡ ተከራካሪ ወገኖች ዳኛ የመሾም መብታቸውን ጠብቀው ተቋሙ ግን ጉዳዩን እንዲያስተናግድላቸው ብቻ መብታቸውን የሚጠብቁበት ሁኔታዎች ያጋጥማሉ፡፡ በእንደዚህ ዓይነት አጋጣሚዎች ተቋሙ በተቻለ ፍጥነት የአሿሿሙ ስርዓት ከተቋሙ መደበኛ አሰራር ጋር ወጥነት ያለው እንዲሆን ለማድረግ ዓላማ ያለው ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፡፡ በዚህም መሰረት በተከራካሪ ወገኖች የተሾሙ የግልግል ዳኞች በተቋሙ እንደሚሾሙ የግልግል ዳኞች አግባብ ባለው የምክር ቤቱ ደንብ መሰረት በተመሳሳይ ስርዓት የግልግል ዳኝነትን ስለመቀበላቸውን እና ከተከራካሪ ወገኖች፣ከጠበቆቻቸው እና ከጉዳዩ ጋር አስቀድሞ ምንም ዓይነት ግንኙነት የሌላቸው እና ነፃ መሆናቸውን የሚያረጋግጡበት ቅፅ እንዲሞሉ ይገደዳሉ፡፡ የዚህ ዓላማውም የተሿሚዎችን ነጻነትን እና ገለልተኝነት ለማረጋገጥ ነው፡፡

የኢትዮጵያ የፍትሐ ብሔር ህግ የግልግል ዳኞችን ነፃነት እና ገለልተኝነት ለማረጋገጥ የሚያግዝ ጠቃሚ የሆኑ ድንጋጌዎችን አስቀምጧል፡፡ በእነኚህ ድንጋጌዎች መሰረት አንድ የግልግል ዳኛ ለፍርድ ቤት በሚቀርብ ጥያቄ መሰረት ለስራው የማይመጥ ሆኖ ከተገኘ ሊወገድ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ በግልግል ተቋም ቁጥጥር በማይደረግባቸው ጊዚያዊ ግልግሎች ላይ የሚሰሩ የግልግል ዳኞች ከመሾማቸው በፊት ምን ዓይነት የማጥራት ስርዓት እንደሚያልፉ ግን ግልፅነት የለውም፡፡ በግልፅ እንደሚታየው ተቋማዊ ግልግልን በሚያስፈፅም አካል ዘንድ ያለውን እና ከፍ ተብለው የተብራሩት ስለ ግልግል ዳኞች አሿሿም የተደነገጉት ዝርዝር ሥነ ሥርዓቶች እና ህጎች በጊዚያዊ ግልግል ላይ አይኖሩም፡፡

በዝርዝር የግልግል ዳኞች፣ የአግባቢዎች፣ የአስማሚዎች እና የአድጁዲኬተሮች አሰያየም እና አሿሿም ስርዓቶች ላይ ምርጫቸውን የጣሉ ተከራካሪ ወገኖች በእርግጠኝነት ሌላ ቦታ ዝግጁ ሆነው በማይገኙ ወይም በሌሉ ግልፅነት እና ተጠያቂነት ያላቸው አገልግሎቶችን ለማግኘት ዋስትና አላቸው፡፡